# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

# ዲጂታል ዜና መጽሔት

ቁጥር 5 መጋቢት 2016 ዓ.ም


## አዲስ የተሾሙት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ከነባርና አዲስ የቦርድና የማኔጅመንት አባላት ጋር ትውውቅ አደረጉ






የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው አዲስ የተሾሙት የኢ.ፌድሪ ጠቅላይ ሚንስትር የፋይናንስ ዘርፍ አማካሪ ሚንስትር ክቡር አቶ ተክለወለድ አጥናፉ ከባንኩ ነባርና አዲስ የዳይሬክተሮች ቦርድና የማኔጅመንት አባላት ጋር ትውውቅና ውይይት አካሄዱ።

ሐሙስ የካቲት 28 ቀን 2016 ዓ.ም የተካሄደው ትውውቅ ከዚህ ቀደም በተጓደሉት የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ምትክ አዲስ ከተሾሙት አራት የቦርድ አባላት እንዲሁም ባንኩን በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት እያገለገሉ ከሚገኙ አባላትና ከባንኩ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ነው።

በዕለቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

በመቀጠልም የባንኩ ፕሬዚዳንት አዲስ ለተሾሙት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለ ኢትዮጵያ ልማት ባንክ አጠቃላይ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ እና አፈፃፀም ገለፃና ማብራሪያ አድርገውላቸዋል።

በተለይ ባንኩ ገጥሞት ከነበረው ችግር ወጥቶ ዛሬ ላይ ለደረሰበት የተሻለ አፈፃፀምና በተከታታይ እያስመዘገበ ላለው ውጤት በመንግስት የተወሰደው እርምጃ፣ በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ወደ ሥራ የገባው የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ማኔጅመንት እና ሠራተኞች ጥረትና የሪፎርም ትግበራ ወሳኝ እንደነበሩ ፕሬዚዳንቱ ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው አዲስ የተሾሙት ክቡር አቶ ተክለወለድ አጥናፉ በበኩላቸው፣ ባንኩን ከነበረበት ችግር ለማውጣት በመንግሥት፣ በቦርዱና በማኔጅመንት የተወሰደው እርምጃ ውጤት ማምጣቱን ጠቁመው በቀጣይ ዓመታት ባንኩ ለሀገራችን ልማት የሚኖረውን ድርሻ ከፍ ለማድረግ 2ኛ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅትና ትግበራ በልዩ ትኩረት በመሥራት ለውጥ ለማምጣት እንደሚሠሩ አስታውቀዋል።

አዲስ የተሾሙት የቦርድ አባላትም በተደረገላቸው መልካም አቀባበል አመስግነው ስለ ባንኩ በቀረበው አጠቃላይ ገለፃ ለቀጣይ ሥራቸው ግብአት የሚሆን ግንዛቤ ማግኘታቸውንና በቀጣይ የሥራ ዘመናቸው በሚኖራቸው ቆይታ የበኩላቸውን አመራር በመስጠት፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በትኩረት ባንኩ የተሰጠውን ተልዕኮ እንዲወጣ የበኩላቸውን እንደሚወጡ ገልፀዋል።



# የባንኩ የስድስት ወራት አፈጻጸምን በማስመልከት በየደረጃው ያሉ የባንኩ አመራሮች የተሳተፉበት ሰፊ ውይይት ተካሔደ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የስድስት ወራት አፈጻጸምን በማስመልከት የማኔጅመንት አባላት፣ ሥራ መሪዎች፣ የዲስትሪክት እና ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች የተሳተፉበት ሰፊ ውይይት በባንኩ መሰብሰቢያ አዳራሽ ለሦስት ቀናት ተካሔደ።

ከየካቲት ሰባት እስከ የካቲት ዘጠኝ ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው በዚህ ሰፊ የውይይት መድረክ የባንኩ የማኔጅመንት አባላት፣ ሥራ መሪዎችና ዲስትሪክት ሥራ አስኪያጆች የየራሳቸውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ የተደረገ ሲሆን፣ በዚያ ላይ በመመሥራት ለቀጣይ ስደስት ወራት ግብዓት የተገኘበት ጥልቅ ውይይት ተካሒዷል።

ይኸው የባንኩ ፕሬዝዳንት የመሩት መድረክ የባንኩ አፈጻጸም በዋና መሥሪያ ቤት፣ በዲስትሪክቶችና በቅርንጫፎች በየጊዜው እየተሻሻለ ከመምጣቱ ባሻገር ከፍተኛ ውጤት እየተመዘገበበት መሆኑ ተነሥቷል፡ ፡ በጀመረው የሪፎርም እንቅስቃሴ በብድር ማጽደቅ፣ በብድር መልቀቅ እና በብድር መሰብሰብ በኩል ከጊዜ ጊዜ ውጤታማ እየሆነ የመጣው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በተለይም በብድር መሰብሰብ በኩል እያሳየ ያለውን ጥንካሬ የበለጠ ማጎልበት እንዳለበት በውይይቱ ተመላክቷል።

መድረኩ ድክምት ያሳዩ የሥራ ክፍሎችና ዲስትሪክቶች በመጪው





ስደስት ወራት እንዲጠናከሩ፣ በአፈጻጸማቸው የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ ደግሞ ውጤታቸውን የበለጠ እንዲያጎለብቱ ማሳሰቢያ የተሰጠበት ነበ። ዲስትሪክቶችና ቅርንጫፎች በክልል እና በየደረጃው ካሉ የመንግሥት አካላት ጋር በቅርበት በመሥራት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በስፋት እንዲሠሩ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው አሳስበዋል።

በመጨረሻም በስድስት ወራት በነበረው አፈጻጸም የተሻለ ውጤት ያስመዘገበው የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ኃላፊዎችና ሠራተኞች የገንዘብ ሽልማትና የእውቅና የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል።

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አመራሮች እና በክልሉ ከሚገኙ ባለሀብቶች ጋር ውይይት አካሄደ።



የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሥራ አመራር አባላት ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከፍተኛ የመንግስት አመራሮች ጋር የካቲት 22 ቀን 2016 ዓ.ም በቤንሻንጉል ክልል በአሶሳ ከተማ ውይይት አካሄደ።

የክልሉ ርእሰ መስተዳድር የተከበሩ አቶ አሻድሊ ሐሰን ውይይቱን በንግግር በከፈቱበት ወቅት እንደተናገሩት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት ከክልሉ አመራሮች ጋር ለመወያየት አሶሳ ድረስ በመምጣት ላሳየው ቁርጠኝነት ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

አቶ አሻድሊ በንግግራቸው «በክልሉ ያለውን የባለሀብቱን ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ፍላጎት በተለይም በማእድን እና የግብርና ዘርፍ የመሰማራት ፍላጎትና በክልሉ የሚታየውን መነቃቃት በማየት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከክልሉ ጋር ለመሥራት መነሣቱ ባንኩ ሀገራችንን ለመቀየር እያደረገ ያለው ጥረት ማሳያ ነው>> ብለዋል።



የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው በበኩላቸው <<በብዙ ውጣውረዶች ውስጥ አልፎ አሁን ላይ በከፍተኛ ለውጥና በጥሩ አቋም ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሠራባቸው ክልሎች ውስጥ አንዱ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መሆኑን ገልፀው፤ ከዚህ በፊት በቅርንጫፍ ደረጃ ብቻ የነበረው አገልግሎት አሁን በዲስትሪክት እንዲዋቀር እና ተጨማሪ 3 ቅርንጫፎች በክልሉ እንዲኖሩት ተደርጓል» በማለት በተለያዩ ዘርፎች ወደ ሥራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ለሚገኙና ከባንኩ ጋር ለመሥራት ፍላጎት ላላቸው ሁሉ ምቹ ሁኔታን እየፈጠረ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ፕሬዝዳንቱ አክለውም በአሁኑ ወቅት ባንኩ ግብርናውን በልዩ ሁኔታ ለማሳደግ በግብርና ፕሮጀክት ለሚሰማሩ ደንበኞች ከፍተኛ የወለድ ምጣኔ ማሻሻያ በማድረግ ወደ ሰባት በመቶ ዝቅ እንዲል መደረጉ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች መልካም አጋጣሚ መፍጠሩንም ጠቁመዋል።

በክልሉ ርእሰ መስተዳድር ጽ/ቤት በተዘጋጀው ውይይት በዋናነት ከዚህ በፊት ባንኩ በክልሉ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የሰጠው ብድር የመንግስትና የህዝብ ሀብት በመሆኑ ባንኩ ለማስመለስ የሚያደርገውን ጥረት የክልሉ መንግስት ድጋፍ ማድረግ በሚችልበት ሁኔታ ላይ ምክክር የተደረገ ሲሆን በመድረኩ መግባባት ላይ መደረሱም ተጠቅሷል።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንትና የማኔጅመንት አባላት በቤንሻንጉል ክልል ከሚገኙ ባለሀብቶች ጋር በአሶሳ ከተማ ሰፋ ያለ ውይይት ያካሄዱ ሲሆን፣ በውይይቱ መድረክም የክልሉ ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊን ጨምሮ የሚመለከታቸው የክልሉ ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል።

ከባለሀብቶች ጋር በተደረገው በዚህ የውይይት መድረክ የታደሙ ባለሃብቶቹ ባንኩ ትኩረት በመስጠት የውይይት መድረክ ማዘጋጀቱና ተቀራርቦ ለመስራት የሚያስችል ምክክር እንዲኖር ማድረጉን አመስግነው ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎችንና በባንኩ ዙሪያ ያላቸውን አስተያየቶች አቅርበዋል።

ባንኩ በክልሉ ውስጥ በኢንቨስትመንት ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ሁሉ አሰራሩንና የብድር አቅርቦቱን በዲስትሪክት ደረጃ እስከ 85 ሚሊዮን ብር እንዲጸድቅ አቅም መፍጠሩን ጠቁመው የብድር ማጽድቅ ሂደቱን ለማሳጠር የተሰሩ ስራዎች የበለጠ ቀልጣፋና በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ፕሬዝዳንቱ አስታውቀዋል።




# ባንኩ ለሊዝ ፋይናንስ ደንበኞቹ 49 ተሽከርካሪዎችን አስረከበ



**የኢትዮጵያ ልማት ባንክ** ለሊዝ ፋይናንስ ደንበኞቹ 49 ዘመናዊ ተሽከርካሪዎችን ማክሰኞ የካቲት 5 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ቢሾፍቱ ሃግቤስ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ግቢ ውስጥ አስረክቧል።

ባንኩ ያስረከባቸው ዘመናዊ ተሽከርካሪዎች 28 ለቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን፤ ለግንባታና ማዕድን ልማት የሚያገለግሉ 14 ኤክስካቫተር እና 7 ሎደሮችንም አስረክቧል።

ባንኩ በትናንትናው እለት ያስተላለፋቸው ኤክስካቫተር ማሽኖች 89 ሚሊዮን ብር፣ ሎዶሮቹ 21.1 ሚሊዮን ብር እና በቱሪዝም ዘርፍ ለተሰማሩ ደንበኞች የተላለፉት ዘመናዊ ተሽከርካሪዎች ደግሞ 69 ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገባቸው መሆኑን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው በርክክብ መርሐ ግብሩ ላይ አብራርተዋል።



ከአራት ዓመታት በፊት በዚህ ዘርፍ ይሰጥ የነበረው 4 ነጥብ 3 ቢልዮን ብር ብድር እንደነበር ያስታወሱት ዶ/ር ዮሐንስ ዘንድሮ በስድስት ወራት ብቻ 10 ቢሊዮን ብር ብድር መስጠት መቻሉንና የሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት ከፍተኛ እድገት እያሳየ መሆኑን ተናግረዋል፡ ፡ ይህም ባንኩ ከሪፎርም በፊት ከነበረበት ሁኔታ በመውጣት ስኬታማ ሥራ እየሠራ መሆኑን አመላካች ነው ብለዋል።

ባንኩ በቱሪዝም፣ በኮንስትራክሽን እና በማዕድን ዘርፎች ላይ ለተሰማሩ ዜጎች የሚያደርገው ድጋፍ በየጊዜው እያደገ መምጣቱ በርክክብ ወቅት ተመላክቷል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ባደረገው የሪፎርም ሥራ ተደራሽነቱን ማስፋት የቻለ ሲሆን፣ በፕሮጀክት እና ሊዝ ፋይናንሲንግ የብድር ሞዳሊቲ የላቀ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸውን ዘርፎች በመለየት እና በመደገፍ ውጤታማ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ■

# የተተከሉ ችግኞች ያሉበትን ሁኔታ የሚገመግም የጉብኝት መርሐ ግብር ተካሔደ



የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር እና ተጠሪ ተቋማት በጋራ የተከሏቸውን ችግኞች ያሉበትን ሁኔታ የሚገመግም የጉብኝት መርሐ ግብር አርብ የካቲት 22 ቀን 2016 ዓ.ም በሞጆ ሐዋሳ የፍጥነት መንገድ መግቢያ አካበቢ በሚገኘው መትከያ ሥፍራ ተካሔደ።

በዕለቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ኃ/ሚካኤል <<የተሠራው ሥራ የደረሰበትን መገምገምና ቀጣይ ክፍተቶችን አርሞ ለሌላ ሥራ መዘጋጀት ተገቢ በመሆኑ ጉብኝቱ ተዘጋጅቷል>> በማለት የጉብኝቱን ዓላማ አስረድተዋል። <<ለሌሎች ተቋማት አርያ በሚሆን መልኩ ሥራዎች በጥንቃቄና በእቅድ በመሠራታቸው ፓርኮችን ማልማት ተችሏል>> ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ << በጀት በመመደብና በዕቅድ ተካቶ በመሠራቱ አመርቂ ውጤት ተገኝቷል። በቀጣይም ከዚህ የበለጠ ትኩረት ይደርግበታል >> ብለዋል። የኢትዮጵያ ልማት ባንክ(ኢ..ል.ባ) የማኔጅመንት አባላትን ጨምሮ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ተጠሪ ተቋማት ሥራ ኃላፊዎች በተሳተፉበት ጉብኝት በኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች በኩል በተደረገው እንክብካቤና ጥበቃ በክረምት ወራት የተተከሉት









ችግኞች  ሙሉ በሙሉ በሚያስብል ደረጃ መጽደቃቸውም ተገልጿል።

ከጉብኝቱ በኋላ በተደረገው ውይይት ወቅት የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሙስጠፋ አባሲመል <<የተሰጠን አደራ በአግባቡ በመወጣት ችግኞችን ተንከባክበን ማሳደግ ችለናል>> ብለዋል። <<በክረምቱ የተከላ ወቅት የተተከሉትን በልዩ ትኩረት ስንከባከባቸው ቆይተንናል>> ያሉት ኃላፊው ለቀጣዩ የተከላ መርሐ ግብር የሚሆን ከ140 ሺሕ በላይ በላይ ችግኞች ለተከላ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል። ራስ አቅም ችግኝ ማዘጋጀት መቻሉ ወጭን ከመቀነሱ ባሻገር የአካባቢውን የአየር ሁኔታ ቀድመው የተላመዱ በመሆናቸው ለመጽደቅ እንደማይቸገሩም አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝደንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው <<በዚህ ወቅት የሥራችንን ውጤት በአካል ተገኝተን ማየታችን ለቀጣይ ሥራ የሚያበረታታን ነው፤ የተሠራው ሥራ ከሀገር አልፎ ለአፍሪካ ነው ያሉት ፕሬዝዳንቱ በቀጣይ የችግኝ ተከላና እንክብካቤ አጠናክሮ ሥራውን ለማስቀጠል ባንኩ ዝግጁ ነው>> ብለዋል።  እንደ ችግር ለተነሣው የውኃ አቅርቦት ማነስም ጥልቅ ጉድጓዶችን ተባብሮ መቆፈር ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ዮሐንስ ይህን በጋራ ማሳካት ከቻልን ከችግኞች አልፎ ለአካባቢው ማኅበረሰብም ተጨማሪ አገልግሎት የሚሰጥ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ያስችላል። በተጨማሪም ሌሎች አዳዲስ ሥራዎችን በመሥራት፣ እንክብካቤውን በማስቀጠል ለትውልድ ቅርስ የሚሆን ሥራ በጋራ እንሠራለን>> ብለዋል።

ሐምሌ 27 ቀን 2023(እ.አ.አ) ኢ..ል.ባ ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ጋር በመተባበር በሞጆ ሐዋሳ የፍጥነት መንገድ በርካታ የባንኩ ሠራተኞች በተሳተፉበት ችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ማካሔዱ የሚታወስ ሲሆን፣ አሁንም የችግኞቹን አስተዳደግ ሁኔታ ለመገምገም በተዘጋጀው የጉብኝት መርሐ ግብር ተሳታፊ ሆኗል።

# <<ውጤት እንዲመዘገብ የሥራ መሪነት ኃላፊነቴን ለመወጣት የሚቻለውን ሁሉ አድርጌአለሁ>> - አቶ ጌትነት ተመቸው

የኢ.ል.ባ ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር




የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የ2023/24 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለመገምገም ከየካቲት 7-9 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ በተሳታፊዎች እና በከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት ግምገማ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የላቀ አፈጻጸም በማምጣቱ ከፍተኛ ምስጋናና ዕውቅና ተቸሮታል። በዚህ ለሥራ ክፍሉ ዳይሬክተርና ለመላው የክፍሉ ሠራተኞች በተሰጠው እውቅና ምስጋናና ሽልማት በተመለከተ ከሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጌትነት ተመቸው ጋር የቃለ ምልልስ ቆይታ አድርገናል። እነሆ፦

ጥያቄ፦ በቅድሚያ ራስዎን ቢያስተዋውቁን፤

አቶ ጌትነት:- አመሰግናለሁ፤ ጌትነት ተመቸው መኰንን እባላለሁ፤ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ኮርፖሬት የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ነኝ።

ጥያቄ፦ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ማኔጅመንት የሥራ ክፍላችሁ በ2023/24 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ሥራ አፈጻጸም ግምገማ መድረክ ከተሳታፊዎችና ከባንኩ የማኔጅመንት አባላት ለተሰጣችሁ ምስጋና እና እውቅና የባንኩ የሚዲያና ኮምዩኒኬሽንስ ዳይሬክቶሬት የተሰማውን ደስታ በዚሁ አጋጣሚ እየገለጸ በተገኘው ምስጋና፣ እውቅናና ማበረታቻ ሽልማት ምን ተሰማዎት? ዘርዘር አድርገው ቢገልፁልኝ፤

አቶ ጌትነት ፡- ፍፁም የሆነና ያልተጠበቀ ደስታ ነዋ! ካሉ በኋላ በመቀጠል የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የልማት ብድሮችን የሚያቀርብ የፋይናንስ ተቋም እንደመሆኑ መጠን በሥራው ውጤታማ ይሆን ዘንድ ማንኛውም የብድር ጥያቄ የባንኩን ፖሊሲና ፕሮሴጀር መከተልና የብድር መመዘኛ መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፤ የብድር አሰጣጥና አመላለስ ራሱን የቻለ የፋይናንስ ጥበብ ስላለው ጤናማ ብድር መስጠት (Prudent Lending) የተበላሸ ብድር እንዳይኖር ያደርጋል።

ለዚህም ዓላማና ግብ ሲባል ከፍተኛ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ሕግን ተከትሎ የማበደር ሥራ መሥራት እንዲቻል የሥራ ክፍላችን ያልተቋረጠ (ያላሠለሰ) የሕግ ምክርና ድጋፍ ይሰጣል/ሰጥቷል።

እንደሚታወቀው የሥራ ክፍላችን ደንበኞች ከቅርንጫፍ እስከ ዋናው መሥሪያ ቤት ያሉ የሥራ ክፍሎች ናቸው። እነዚህ ደንበኞቻችን (በተለይም አበዳሪ የሥራ ክፍሎች) የእኛን የሕግ ምክር ድጋፍ በአግባቡ መጠቀማቸው ባንኩ ለስጋት (Legal Risk) ተጋላጭ እንዳይሆንና ጤናማ ብድር እንዲሰጥ እና እንዲመለስ የራሳችንን አዎንታዊ ተጽዕኖ እያደረግን እንገኛለን፤ ይህ እውነታ (ፈጣን፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት) በደንበኞቻችን በአጠቃላይ በማኔጅመንቱ በተለይ ትኩረትና ክብደት አግኝቶ (በሰጠነው አገልግሎት ረክተው) እውቅና በመሰጠቱ እንደ ሥራ መሪ ወደርየለሽ ደስታ ተሰምቶኛል።

ጥያቄ፦ ክፍላችሁ በዚህ ደረጃ ለመመስገን የበቃው ምን ምን ተግባራትን በማከናወኑ ነው?

አቶ ጌትነት፦ ተግቶ ለውጤት መሥራት መጨረሻው መልካም እንደሚሆን እናምናለን። ከዚህ አንጻር ባንኩ የለውጥ ሥራዎችን በአዲስ መልክ መተግበር ከጀመረበት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ከሚዛናዊ የሥራ አፈጻጸም መለኪያ (BSC) አንፃር ከባንኩ ተቆርሶ ለሥራ ክፍላችን የተሰጡ ቁልፍ ሥራዎች አሉ፤ እነዚያም ፕሮጀክት ፋይናንሲንግ እና ሊዝ ፋይናንሲንግ ላይ ያተኮሩ ናቸው። የእኛም አገልግሎት በእነዚህ ላይ ያነጣጠረ ነው።

ከዚህም በቀር በታክስ፣ በሠራተኛ ጉዳይ እና በሌሎች ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ዙሪያ የምክር አገልግሎት በመስጠት ባንኩን እናገለግላለን። ከሕግ የምክር ድጋፍ አገልግሎት ባልተናነሰ (Last but not least) ባንካችን ሲከሰስ፣ ሲከስም ሆነ ጣልቃ ሲገባ በመደበኛ ፍርድ ቤቶችና በሌሎችም አካላት የባንኩን መብትና ጥቅም በማስጠበቅ/በማስከበር ረገድ ሊተካ

የማይችል ሚና ይጫወታል፤ በዚህ ረገድ የሥራ ክፍላችን እጅግ አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ ማኔጅመንቱን አስደስቷል።

**ጥያቄ፦ በተገኘው የምስጋና እና እውቅና ሽልማት የክፍሉ ሠራተኞች ስሜት ምን ይመስል ነበር?**

**አቶ ጌትነት፦** እንዲህ ዓይነቱ ዕውቅና አሠጣጥ በባንካችን ያልተለመደ ስለሆነ ሁሉም የክፍሉ ሠራተኞች ከፍተኛ እርካታ ተሰምቷቸዋል፤ በዓርዓያነቱም ለሁሉም የባንኩ ማኅበረሰብ ትምህርት ሰጪ ሆኖ አልፏል።

**ጥያቄ፦ እርስዎ እንደ ሥራ ክፍል መሪ ያደረጉት አስተዋጽኦ ምን፣ ምን ነበር?**

**አቶ ጌትነት፦** በመጀመሪያ ደረጃ ከክፍሌ ሠራተኞች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለን፤ የቡድን ስሜታችንም ጠንካራ ነው፤ Coaching, Mentoring and Counselling ሁሉም የሥራ መሪ ሊተገብራቸው የሚገባ የሥራ አመራር ጥበቦች ሲሆኑ በእኛ የሥራ ክፍል ጥበቦቹ ከንድፈ-ሐሳብ ባለፈ ፍፁም በሆነ ቁርጠኝነት እና የሥራ ፍላጎት የታጀበ ሠርቶ የማሠራት እንቅስቃሴ በመኖሩ ምክንያት ይህን በማድረግ የሥራ መሪነት ኃላፊነቴን ለመወጣት የሚቻለውን ጥረት ሁሉ ተደርጓል ብዬ አምናለሁ።

**ጥያቄ፦ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በሀገር ልማት ያለውን ጉልህ አስተዋጽኦ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ጌትነት፦** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የመንግሥትን የትኩረት አቅጣጫና የልማት ፕሮግራም ተከትሎ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የልማት ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ብድር በማቅረብ ረገድ በኢንቨስትመንት ባንክነት የገበያ ጉድለትን እየሞላ ለሀገራችን ልማት፣ ዕድገትና ብልፅግና መሠረት የሚጥሉ መጠን ሰፊ ሥራዎችን አከናውኗል።

ይህንኑ ተከትሎ በባንካችን ብድር የሚቋቋሙ የልማት ፕሮጀክቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት፣ በውጭ ተመርተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ በማድረግ ፣ የልማት ፕሮጀክቶቹ ወደ ኦፕሬሽን ከገቡ በኋላ ተገቢውን የመንግስት ግብር በማስገኘት እንዲሁም ባንካችን ተበድሮ የሚያበድር የፋይናንስ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የሰጠውን ብደር በአግባቡና በጊዜው በመሰብሰብ ለቀጣይ ልማት መልሶ ማበደር ብቻ ሳይሆን ዕዳውን በወቅቱ በመክፈልም ጭምር ለሀገር ልማት የሚያደርገው አስተዋፆ ከፍተኛ ነው።

**ጥያቄ፦ የውጤታማነቱ መገለጫ ላይ የተወሰነ አስተያየት ቢያክሉ፤**

**አቶ ጌትነት፦** የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለልማት ፕሮጀክቶች ለሚያቀርበው ብድር ዋስትናው/መያዣው ፕሮጀክቱ ብቻ ነው። በተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ተጨማሪ ዋስትና (Additional/External Collateral) አይጠይቅም።

ከዚህ የተነሣ የብድር አመላለሱ ጤናማ ሳይሆን እየቀረ ባንካችን እስከ 40% የሚደርስ የተበላሸ ብድር ክምችት አጋጥሞት ነበር። ከ2013 ዓ.ም በኋላ ግን ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ የነበረውን የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እና ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት ታስቦ በአዲሱ የባንኩ ሥራ አመራር የለውጥ ሥራዎች በመከናወናቸው ምክንያት በአጭር የጊዜ ገደብ ውስጥ የተበላሸውን የብድር ክምችት ወደ Single Digit (7.3%) ለማውረድ የተቻለ ሲሆን፤ ይህ የላቀ ክንውን በጎላና በተረዳ ነገር የባንኩን ውጤታማነት ፍንትው አድርጎ አሳይቷል።

**ጥያቄ፦ ከ19 ዓመታት በላይ በዚህ ባንክ ሲያገለግሉ በሥራዎ ሂደት የማይረሱት አስደሳች ገጠመኝ ካለ ቢያስታውሱን፤**

**አቶ ጌትነት፦** በእነዚህ ዓመታት ከብዙ በጥቂቱ 3 (ሦስት) አይረሴ ደስታዎችን አስታውሳለሁ፦-

1. ስሙን መጥራት የማያስፈልግ የባንካችን ተበዳሪ/ደንበኛ ነበር፤ ለዚህ ደንበኛ ብድር መመለስ እንደ ጎጂ ተግባር/ ባህል የሚቆጠር ነው። ይህ ሰው በከተማችን ስመ-ጥር ባለሀብት ከሚባሉ መካከል



አንዱ ሲሆን፣ ለረጅም ጊዜ ብድር ሳይከፍል ቆይቶ ነበር። የባንካችን አበዳሪ የሥራ ክፍሎች የብድር መኮንን ወደ ፕሮጀክቱ ሲልኩም ለማናገር ፈቃደኛ አልነበረም። ሠራተኞቹ ወደ ቢሮ ሲሄዱ በጸሐፊው በኩል <<...የባንካችሁን ማኔጅመንት አናግሪያለሁ እያለ ሲያሾፍ ይቆያል...>>

በአጋጣሚ በባንካችን የማኔጅመንት ለውጥ ተደረገና የብድር ፋይሉ ወደ ሥራ ክፍላችን ተላከ/ተላለፈ። የሥራ ክፍላችን በፎርክሎዠር ሕጉ፣ በብድሩ እና በመያዣ ውሉ መሠረት የ30 (ሠላሳ) ቀናት ማስጠንቀቂያ መስጠት ነበረበት፤ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ተበዳሪ ግን ምርጫ ያደረገው ብድሩን በመክፈል ግዴታውን መወጣት ሳይሆን፣ በለመደው መንገድ ሥራ ኃላፊዎችን <<ጊዜ ይሰጠኝ>> ብሎ መጠየቅ ነበር። እኛ ግን ሕጉን መሠረት አድርገን የማስጠንቀቂያ ጊዜው እንደተጠናቀቀ የመያዣ ንብረቱን ኅዳር 26 ቀን 2000 ዓ.ም ለመረከብ ቀን ቆርጠን የመያዣ/የዋስትና መብት መዝጋቢ ለሆነው ክፍለ ከተማ ደብዳቤ ጻፍን።

ክፍለ ከተማው ባንካችን በጠየቀው መሠረት ተወካይ መላክና ለፖሊስ ደብዳቤ መጻፍ ሲገባው ከተበዳሪ ጋር የማይገባ ግንኙነት በመፍጠር ግዴታውን ሳይወጣ ቀረ።

በባንካችን በኩል ጉዳይ ለማስፈፀም የተላኩት የክፍላችን ሠራተኞችም ችግሩ ከአቅማቸው በላይ እንደሆነባቸው ሪፖርት አቀረቡ በዚህ ጊዜ ነበር ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ወደ ክፍለ ከተማው በመሄድ ክፍለ ከተማው በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት ለምን እንደማይወጣ የጠየቅነው፤ ጉዳዩ የሚመለከተው የክ/ከተማው የሥራ ኃላፊ ለምን ሕግ የጣለበትን ኃላፊነት እንዳልተወጣ ሲጠየቅ ተበዳሪው <<...ከባንኩ ማኔጅመንት ጋር እየተነጋገርኩ ስለሆነ ይቆይልኝ ስላለኝ ነው...>> የሚል ምላሽ ሰጠን፤

ከማኔጅመንት አባላት አንዱና ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው እኔን እንደሆነ በመግለፅ ክ/ከተማው በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት ወደ ጎን በመተው የግለሰቡ ጠበቃ በመሆን ለፈፀመው ብልሹ አሠራር በፀረ-ሙስና ኮሚሽን በኩል በህግ ለመጠየቅ እንገደዳለን የሚል ማስፈራሪያ በማቅረብ ወደ ቢሮችን ለመመለስ ስንቀሳቀስ የተጠቀሰው የክ/ከተማ የሥራ ኃላፊ ለፖሊስ ተፅፎ ሳይፈረምበት የቆየውን ደብዳቤ ከጠረጴዛ መሳቢያው በማውጣት በፊታችን ፈርሞ ስለሰጠን ትዕዛዙን ለፖሊስ እንዲደርስ ካደረግን በኋላ ኅዳር 26, 2000 ዓ.ም. ከመድረሱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ርክክብ ሊፈፀም ሲል ያ ብድር ባለመክፈል የሚታወቅ ደንበኛ ለዓመታት ሳይከፍል የቆየውን ውዝፍ የባንክ ወለድ ብር 38,000,000.00

( ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ብር) በአንድ ጊዜ ወዶ ሳይሆን ተገዶ በመክፈሉ ያንን አጋጣሚ ሳስታውሰው የተለየ የደስታ ስሜት ይፈጥርብኛል።

ሁለተኛው አይረሴ አጋጣሚ የቱርክ ባለሀብት የነበረ የባንካችን ተበዳሪ በደብረ ብርሃን ከተማ በሊዝ ውል በተሰጠው 6 ሄክታር ይዞታ የጫማና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካ ያቋቋመ ቢሆንም ብድሩን በወቅቱ መክፈል ባለመጀመሩ ምክንያት በፎርክሎጀር ሕግ፣ በብድር እና በመያዣ ውሉ መሠረት ተረክበን በምናስተዳድርበትና ለሃራጅ ግምት እያዘጋጀን ባለንበት ወቅት፤ ከባንካችን በተሰጠ ብድር የፋብሪካው ሕንፃ መሉ በሙሉ ካጠናቀቀ፣ የአስተዳደር ቢሮ ግንባታን finishing ሲቀር ከጨረሰ፣ የፋብሪካውን ዙሪያ አጥር በግንብ ከሠራ፣ የፋብሪካውን ቅጥር ግቢ የድንጋይ ማስቻታ ሥራ አጠናቆ አስፋልት ማንጠፍ ሲቀረው፣ በፋብሪካው ግቢና ዙሪያው 35 ኮንቴይነር ከውጪ ሃገር የመጣ የፕሮጀክት ዕቃ ተከማችቶ ባለበት ሁኔታ፤ በአማራ ክልላዊ መንግሥት ኢንዱስትሪ ልማት ኮርፖሬሽን የደብረ ብርሃን ቅ/ጽ/ቤት ከከተማው ከንቲባ ጋር በመተባበር የፕሮጀክቱን ይዞታ ያለአግባብ የሊዝ ውል በማቋረጥና የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) በማምከን ባንካችን በዋስትና የያዘውን ይዞታ ሙሉ በሙሉ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ በመወሰን ሳያቆሙ፤ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (ካርታ) ለሌላ ግለሰብ አዘጋጅተው በመስጠታቸው ምክንያት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ያቀረብነው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት ባያገኝም ስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብነው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ውሳኔው በውሳኔ በመሻሩ ምክንያት በሕግ ወጥ መንገድ የተሠራው ካርታ መክኖ ባንካችን ከሦስት ዓመታት እልህ አስጨራሽ ክርክር በኋላ ለብድር አመላለስ በዋስትና የያዘውን ንብረት መልሶ መረከብ በመቻሉ እጥፍ ድርብ ደስታ ተሰምቶናል።

ሦስተኛው ደንቅ አጋጣሚ ደግሞ የሺሕ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ እንደሚባለው የሥራ ክፍላችን በባለቤትነት፣ በኃላፊነት፣ በተቆርቋሪነት እና በአገልጋይነት ስሜት ያከናወነው ሥራ በባንኩ ማህበረሰብ በአጠቃላይ በማኔጅመንቱ ደግሞ በተለይ ዕውቅና አግኝቶ ለሽልማት የበቃንበት የየካቲት 9 ቀን 2016 ዓ.ም ምሽት ለደስታችን ልዩ ማሳረጊያ ሆኖልናል!!!

ጥያቄ፦ ለነበረን የቃለ ምልልስ ቆይታ እናመሰግናለን፤

አቶ ጌትነት፦ እኔም አመሰግናለሁ።

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አመራርና ሠራተኞች ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን አከበሩ



የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አመራርና ሠራተኞች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ 113ኛ፤ በአገራችን ደግሞ ለ48 ኛ ጊዜ የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት አክብረዋል።

“ሴቶችን እናብቃ ልማትንና ሰላምን እናረጋግጥ” በሚል መሪ ቃል በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በተከበረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ላይ የተገኙት የባንኩ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው <<የሴቶች ቁልፍ ተሳትፎ ለሀገር እድገት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።>> ሲሉ መልእክታቸውን ባስተላለፉበት የበዓሉ አከባበር መድረክ ባንኩ ይህንኑ በማመን ባከናወነው ሪፎርም ከ20 በመቶ በላይ ሴቶችን ወደ አመራር ማምጣቱን አረጋግጠዋል።

ኢትዮጵያ ልማት ባንክ መሠረታዊ የሠራተኞች ማኅበር የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ተጠሪ የሆኑት ወይዘሮ ዓለም ስዩም በበኩላቸው ሴቶች ለልማትና ለሰላም አበርክቶ የማይተካ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል።

በፕሮግራሙ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማት ሠራተኞች ማኅበር ኢንዱስትሪ ፌዴሬሽን ም/ፕሬዝዳንት አቶ አበራ ጌታቸው <<ባንኩ በከፍተኛ እድገት ላይ እንደሚገኝ የገለጹ ሲሆን፣ ይህ ስኬት የተመዘገበውም ለሠራተኞች ልዩ ትኩረት በመስጠቱ ነው>> ብለዋል።


የፌዴሬሽኑ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ተጠሪ ወ/ሮ እሌኒ አብርሀም



በባንኩ የተለያዩ ቅርንጫፎችና ዲስትሪክቶች ተዘዋውረው መመልከታቸውን ጠቅሰው ባንኩ ለሠራተኞቹ እየደረገ ለሚገኘው ዘርፈ ብዙ ድጋፉ አመስግነዋል።

በዕለቱ በተዘጋጀው መርሐ ግብር ላይ የባንኩ ከፍተኛ አመራሮች፣ የማኔጅመንት አባላት፣ ሴት ሠራተኞች እንዲሁም ተጋባዥ እንግዶች ተገኝተዋል። ባንኩ ሴቶችን በማብቃትና ወደ አመራር በማሳደግ ለፈፀመው አበረታች ተግባር ከኢትዮጵያ ፋይናንስ ተቋማት ሠራተኞች ማኅበር ኢንዱስትሪ ፌድሬሽን ዕውቅና ተበርክቶለታል።

# ማስታወሻ



የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በዚህ ዓመት ከዚህ ዓላም በሞት የተለዩንን ባልደረቦቻችንን ስናስታውስ በታላቅ ሐዘን ነው።

## ወ/ሮ አዜብ አበበ

በኢትዮጵያ ልማት ባንክ እአአ በ1996 ተቀጥረው ለ28 ዓመታት በተለያዩ ሙያዎችና ኃለፊነት ቦታዎች አገልግለዋል። ሕይወታቸው አስካለፈበት ጥቅምት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በሰሜን አዲስ አበባ ቅርንጫፍ በዲቪዝን ኃላፊ ደረጃ ይሠሩ ነበር።


## አቶ ኃይሉ መንገሻ

በኢትዮጵያ ልማት ባንክ እአአ በ1996 ተቀትረው ለ28 ዓመታት በጥብቃ ሥራ ባንኩን አግልግለዋል። ሕይወታቸው እስካለፈበት መስከረም 11 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በነቀምት ዲስትሪክት ሻምቡ ቅርንጫፍ በመደበኛ ጥበቃ አገልግሎት ይሠሩ ነበር።

የሁሉንም ነፍስ በአጸደ ገነት እንዲያሳርፍ የባንኩ የሥራ አመራር ቦርድ

አባላት፣ የማኔጅመንት አባላትና የመላው ሠራተኞች ምኞት ነው።

# ባለም አቀፋዊ ልማት ባንኮች







በዓለማችን ብሔራዊ የልማት ባንኮች ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ የልማት ሚና ያላቸው ባንኮች አሉ። እነዚህ ባንኮች የየራሳቸው ዒላማ ቡድኖች አሏቸው። ዋና ዋና የሚባሉትን የዓለማችንን ልማት ባንኮች እናስታውሳችሁ።

- የዓለም ባንክ (World Bank)
- የእስያ ልማት ባንክ (ADB)
- የአውሮፓ መልሶ ግንባታና ልማት ባንክ (EBRD)
- እስያ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት ባንክ (AIIB)
- እስላሚክ ልማት ባንክ (IDB)
- ዓለም አቀፍ የገንዘብ ኮርፖሬሽን (IFC)
- አዲስ ልማት ባንክ (NDB)
- የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ (EIB)
- ኢንተር አሜሪካን ልማት ባንክ (IADB)
- ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF)
- ዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር (IDA)
- የዓለም የንግድ ድርጅት (WTO)
- የአፍሪካ ልማት ባንክ (AfDB)
- የማእከላዊ አሜሪካ ባንክ- ለኢኮኖሚ ውሕደት (CABEI)
- የአውሮፓ ኢንቨስትምንት ባንክ (EIB)
- የላቲን አሜሪካና ካሪቢያን ልማት ባንክ (CAF)
- ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት (IFI)
- ዓለም አቀፍ ፈንድ ለግብርና ልማት (IFAD)
- ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ባንክ (IIB)
- የብዙኃ ጎን ኢንቨስትመንት ዋስትና ኤጀንሲ (MIGA)

ጆሴፍ ብሮዝ ቲቶ መንገድ
+251 11 551 1606
+251 11 551 1188/89
1900

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
የልማት አጋርዎ !